# የሪፖርት አጠቃላይ እይታ

በዲስትሪክት አቀፍ ትንተና በሞንትጎመሪ ካውንቲ አሁን ያለው የትምህርት ቤት ወሰን ምን ያህል የ MCPS አገልግሎትን የሚያራምድ እንደሆነ ለመረዳት፣ በትምህርት ቤቶች ውስጥ የተማሪ ልዩነት፣ ለትምህርት ቤቶች ቅርብ መሆንና የተማሪ ክፍል መረጋጋትን ለማመቻቸት ዓላማ እንዳለው ለማወቅ ይፈልጋል። ጥናቱ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ከስፕሪንግ 2019 ጀምሮ የተሠማራበትን ጥረት ያጠናክራል፤ እንዲሁም በዲስትሪክቱ ውስጥ ይበልጥ ትርጉም ያለው ማዋሀድ፣ የብዝሃነት ልዩነቶችን ማክበር፣ ተደራሽነትን ማስፈን፣ ፈጣን ምላሽ የመስጠት ባህልን ያዳበሩ ትምህርት ቤቶችን ለመፍጠር የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶችን የማህበረሰቡ አባላት መረዳት እንዲችሉ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን በቀጣይነት ያሳትፋል።

ይህ ሪፖርት የተገነባው በመጀመሪያው ምእራፍ (Phase 1) ዲስትሪክት አቀፍ የማካለል ጥናት እና ተሳትፎ ትንታኔ በ በጊዜያዊነት የቀረበ ማርች 2020 የታተመ ሪፖርት ትንታኔ ላይ ነው።

# ዲስትሪክት አቀፍ የወሰን ትንታኔ

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ እየጨመረ ያለውን የምዝገባ እና የተማሪ ህብረተሰብ ስብጥርን መነሻ በማድረግ፥ አሁን ላይ ያለው የትምህርት ቤቶች ክልል ክለሳ እንዲደረግ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትምህርት ቦርድ (MCPS Board of Education) ጃኑወሪ 2019 ባሳለፈው ውሳኔ ለሱፐርኢንተንደንቱ መመሪያ ሰጥቷል።[1] በ 2019 ስፕሪንግ ወቅት MCPS ከመራው የሕዝብ ተሳትፎ በመቀጠል በ WXY አማካሪ ቡድን "WXY consultant team" የሚመራ ዲስትሪክት አቀፍ የክልል ትንታኔ በ 2019 ፎል ላይ ተጀመረ።

የዚህ ጥናት ዝርዝር ትንታኔ አስፈላጊነት የሚደገፈው በትምህርት ቤት ሲስተም እና በካውንቲው እየተለዋወጡ ባሉ ሁኔታዎች ምክንያት ነው። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ይህንን ጥናት ከጀመረባቸው ቁልፍ ምክንያቶች ጥቂቶቹ፡-

- የተጨናነቁ/ከአቅም በላይ የያዙ ት/ቤቶች፡- ከግማሽ በላይ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የተጨናነቁ/ከአቅም በላይ የያዙ ናቸው፥ ይህ ማለት የተመዘገቡት ተማሪዎች ብዛት ከፕሮግራሙ አቅም በላይ ነው። በቀጣዮቹ ዓመታትም የምዝገባ ቁጥሩ እየጨመረ እንደሚሄድ ይጠበቃል።
- የተማሪ ስብጥር (demographics) እየተለወጠ መምጣት፡- የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች ስብጥር በአጠቃላይ ሲታይ ከጊዜ ወደ ጊዜ የተለያየ ነው። ባለፉት 20 ዓመታት በትምህርት ቤት ሲስተም የሂስፓኒክ፣ የእስያን አሜሪካውያን እና አፍሪካን አሜሪካውያን የተማሪዎች ብዛት መጠን እየጨመረ መሄዱ ታይቷል። ይሁን እንጂ በዲስትሪክቱ ውስጥ በሞላ የዘር ወይም የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልዩነቶቹ በአግባቡ እኩል አልተዳሰሱም።
- ከትምህርት ቤት ቅርበት ጋር የተያያዙ አዳጋች ሁኔታዎች፡- በካውንቲው ውስጥ የጂኦግራፊያዊና የመጓጓዣ አውታሮች ላይ ያሉት ልዩነቶች ከትምህርት ቤት ቅርበት ጋር በተያያዘ ውስብስብ ሁኔታዎችን ያስከትላሉ። በማግኔት ትምህርት ቤቶችና በምርጫ ፕሮግራሞች ላይ መመዝገብን ሳይጨምር በዲስትሪክቱ ውስጥ ከሚገኙት ተማሪዎች መካከል 45% በመቶ የሚሆኑት በቅርባቸው በሚገኙ ትምህርት ቤቶች አይገቡም።
- የፕሮግራም ፍላጎቶች መቀያየር፡- የተማሪ ህብረተሰብ ስብጥር መለወጥ እና የአጠቃላይ ምዝገባ እያደገ ሲሄድ፥ የዲስትሪክቱ የፕሮግራሞች ፍላጎቶችን ጭምር ይቀይራል። ለምሳሌ፡- እንግሊዝኛ የመጀመሪያ ቋንቋቸው ያልሆኑ ተማሪዎች ምዝገባ እያደገ መሄድ፥ እንግሊዝኛ ለሌላ ቋንቋ ተናጋሪዎች (ESOL) ፕሮግራም የመጨመርን ፍላጎት ያሳድጋል። ሌሎች ተፅዕኖ ያረፈባቸው ፕሮግራሞች ልዩ ትምህርት፣ የቅድመ-መዋእለ ህጻናት/ሄድ ስታርት፣ እና በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የክፍል-መጠን መቀነስ (CSR) የመሳሰሉት ናቸው።

በአራት ምክንያቶች በመመራት—በዚህ ሪፖርት ላይ ሌንስ ተብለው የተጠቀሱ—በ "Policy FAA" እንደተዘረዘረው፥ (አጠቃቀም፥ የብዝሃነት ስብጥር ልዩነት፥ ቅርበት፥ እና የምደባ አለመዋዠቅን)፥ መሠረት በማድረግ ይህ ዝርዝር ጥናት ወደፊት MCPS እነዚህን እና ሌሎች ችግሮችን ለመቅረፍ የሚያስችሉ ከትምህርት ቤት ማካለል ጋር የተገናኘ እቅድ መዘርጋት እንደሚችል ለትምህርት ቦርድ ግንዛቤዎችንና የጥናት ውጤቶችን አስጨብጧል።

---

1 ማሳሰቢያ: - ከ2007-2008 የትምህርት ዓመት ወዲህ እየጨመረ የነበረው የት/ቤት ምዝገባ በ 2020-2021 የትምህርት ዓመት በኮቪድ-19 ምክንያት ቀንሷል።

## የመጀመሪያ ምዕራፍ (Phase 1) አጠቃላይ እይታ

ከ 2019 ፎል እስከ 2020 ስፕሪንግ ባለው ምዕራፍ 1 (Phase 1) የመረጃ ትንተናን፣ የምርጥ ተሞክሮ፣ ሞዴል እና ሕዝባዊ ተሳትፎን ያካተተ ሲሆን፣ ማርች 2020 ዲስትሪክት አቀፍ የማካለል ትንተና ጊዜያዊ ሪፖርት ለንባብ በማብቃት ተደምድሟል። ከ 2,200 በላይ የማህበረሰብ ዓባላት በየአካባቢው ሰፋፊ ህዝባዊ ስብሰባዎች ላይ የተሳተፉ ሲሆን፣ ተገቢ ውክልና ያላገኙትም በአነስተኛ የቡድን ስብሰባዎች እና የባለድርሻ አካላት ቃለመጠይቆች ላይ ተሳትፈዋል።

ከምእራፍ አንድ (Phase 1) ጥናታዊ ትንተና ሰፋ ያሉ ግንዛቤዎች ተገኝተዋል፥ ይኼውም፡-

- እያንዳንዱ የትምህርት ቤት ደረጃ ከትምህርት ቤት ክልል አንጻር ለየት ያሉ ተፈታታኝ ሁኔታዎችን እና ያሉትን እድሎች ገልጿል። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለተማሪ ለኖራቸው ከሚገባው ቅርበት አንጻር ችግር አለባቸው፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ 2026 ከፍተኛ የሆነ የመጨናነቅ ችግር ይገጥማቸዋል፣ እና የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ደግሞ በአራቱ የትንተና ሌንሶች በጣም ያልተመጣጠነ ልዩነት እንደሚታይ አቅርበዋል።
- ጂኦግራፊ (የህዝብ ብዛት እና እንደ ኢንተርስቴት 270 ለመሻሰሉ ቁልፍ የትራፊክ ኮሪደሮች የሚኖረውን ቅርበት ጨምሮ) በጣም አስፈላጊ እና በ MCPS ዲስትሪክት ትምህርት ቤት ክልሎች በአጠቃላይ በተለያዩ ሜትሪክስ ውጤቶች ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ይኖረዋል።
- በዲስትሪክቱ ሁለት ኮንሰርቲየሞች ያቀረቡት የተለየ እቅድ እሳቤዎች በኮንሰርቲየም (DCC) የዘር ሃረግ እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊን ተከትሎ ከፍተኛ አለመመጣጠን እና በኖርዝኢስት ኮንሰርቲየም (NEC) ከቅርበት ጋር የተያያዘ የበለጠ አስቸጋሪ ሁኔታን አቅርበዋል። [1]
- በ MCPS ውስጥ የሚማሩት (የሚሳተፉት) አካባቢዎችና መዋቅር አሠራር ትምህርት ቤትን ከመከለል አንጻር አስፈላጊ የሆኑ ትልቅ ሚናዎችን ይጫወታል። ለምሳሌ ያህል፣ በክላስተር ማሰባሰብ በዘራቸውና በማኅበራዊ- ኢኮኖሚ ረገድ ልዩነት እንዳይቀንስ አስተዋጽኦ ሊያደርግ ይችላል፤ በአንጻሩም በዘር ወይም በማኅበራዊ ኑሮ ረገድ ያለው ዝቅተኛነት ወደ ትምህርት ቤት የሚጓዙበትን ርቀት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየራቀ እንዲሄድ አስተዋጽኦ ሊያደርግ ይችላል።

በተጨማሪም፥ በምርጥ ተሞክሮ ሞዴል አማካይነት ትንተናው MCPS ን በሀገሪቱ ከስድስት ዲስትሪክቶች ጋር አነጻጽሯል። እነዚህም፡- Charlotte-Mecklenburg Schools (CMS), Duval County Public Schools (DCPS), Fairfax County Public Schools (FCPS), Gwinnett County Public Schools (GCPS), Houston Independent School District (HISD), and Wake County Public Schools (WCPS) ናቸው።

በተጨማሪም ከምእራፍ 1 (Phase 1) ተሳትፎ የተገኙት ግንዛቤዎች ለምእራፍ 2 (Phase 2) የተሳትፎ እና ትንተና አቀራረብ ግንዛቤ አስገኝቷል። እነርሱም የሚያጠቃልሉት፡-

- ይህ ጥናት ያለውን ጠቀሜታ በተመለከተ እርስ በርሳቸው የሚጋጩ አመለካከቶች ነበሩ፤ ይሁን እንጂ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ወደፊት የትምህርት ቤት ድንበሮችን በማስተካከል ረገድ ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡ ነገሮች አሉ።

---

1 አለመመሳሰል፣ ልዩነት አንድ ትምህርት ቤት ከአቻዎቹ ቡድን የተለየ መሆኑ ሲመዘን የሚያሳይ ስታትስቲካዊ መለኪያ ነው (ይኼውም፡- 3 በቅርበት የሚገኙ ት/ቤቶች)። አለመመሳሰል ማለት የሚገለጸው በ 0 እና 1 መካከል ያለ ዋጋ (value) ሲሆን የሚገለጸው – 1 በጣም ልዩነት የሚታይበት ማለት ነው። ስለ ልዩነት/አለመመሳሰል እና በዚህ ትንተና እንዴት ጥቅም ላይ እንደዋለ የተሟላ ማብራሪያ ለማግኘት እባክዎ ጊዜያዊ ሪፖርት (ገጽ 136, 207) ይመልከቱ።

- ዲስትሪክቱ ባለው የህብረተሰብ ስብጥር ተገቢ ውክልና የሌላቸው ቡድኖችን ለመድረስ ባሉት ችግሮች ምክንያት ሰፋ ያለ ተሳትፎ ያልታየበት ግንዛቤ አጠቃላይ ገጽታን የሚያንጸባርቅ አይደለም። ተገቢ ውክልና ያላገኙ ማህበረሰቦችን ለማሳተፍ የሚደረጉ አነስተኛ ስብሰባዎች ቅድሚያ ሊሰጣቸው ከሚገቡ ነገሮች ወይም ቁልፍ የሆኑ ጭብጦች ይልቅ በአካባቢ ህብረሰብ የተለዩ ጉዳዮች ላይ እያተኮሩ የስብሰባ ጭብጦቹም ሌሎች አቅጣጫዎችን የመያዝ ውጤት አላቸው።

- የማህበረሰብ ተሳትፎ ሒደትን በሚመለከት ተደጋግሞ የሚነሣው አንድ ጉዳይ የት/ቤቶች ቅርበት ሁኔታ ነው። ብዙ ወላጆች ለዚህ ሌንስ የሚሰጡት ትኩረት፣ በምእራፍ 2 (Phase 2) ትንተና የሞዴሎቹ አቀራረብ የሚለወጡት በተጠጋጉ ትምህርት ቤቶች አካባቢ ብቻ እንደሆነና አዲስ ዓይነት የማካለል ሞዴልን የሚገድብ መሆኑን ለማወቅ አስችሏል።

- የብዝሃነት ልዩነቶች በትምህርት ቤት ማካለል ለኖራቸው ስለሚገባው ሚና እንዲሁም ስለ ብዝሃነት ልዩነቶች፣ ቅርበት፣ እና ምደባዎች በመካከላቸው ስለሚኖረው የማቻቻል/የማካካስ ሁኔታ የሚጣረሱ አመለካከቶች ነበሩ። በምዕራፍ 2 ትንታኔ በሚሰጥበት ወቅት እንዲህ ያሉ ግንኙነቶች ይበልጥ ቅኝት ተደርጎባቸዋል።

ስለ ምእራፍ 1 (Phase 1) ትንተና እና የማህበረሰብ ተሳትፎ በሚመለከት ሙሉ የማጠቃለያ ግንዛቤ ለማግኘት እባክዎ ምዕራፍ 1 አጠቃላይ ግንዛቤዎች/Phase 1 Overview of Insights ይመልከቱ። አንባቢዎች ይህን ዘገባ በተመለከተ የተሟላ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ከምዕራፍ 1 (Phase 1) ጀምሮ ያሉትን ጥናታዊ ዘገባዎች በስፋት እንዲመለከቱ ይበረታታሉ።



ዲሰምበር 4/2019 በጠረጴዛ ዙርያ በጌትስበርግ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የተደረገ ሪጅናል ህዝባዊ ስብሰባ ዙርያ  የተካሄደ ውይይት ላይ ተሳታፊዎች (photo credit: Rodrick Campbell)

# የሁለተኛ ዙር (Phase 2) አጠቃላይ እይታ

ምእራፍ 2 (Phase 2) የማካለል ጥናት ትንተና የተገነባው በምእራፍ 1 (Phase 1) ጥናትና ተሳትፎ ትንተና ላይ ተመስርቶ ነው።

## ትንተና

በምእራፍ 1 (Phase 1) የተካሄደው የእያንዳንዱ ሌንስ ትንታኔ ከ MCPS መመሪያ እና ከማህበረሰብ ተሳትፎ ከተገኙት እሳቤዎች ጋር ተዳምሮ፥ ለዚህኛው ምእራፍ አቀራረባችን የተሻለ ግንዛቤ አስጨብጦናል። የምእራፍ 1 (Phase 1) እያንዳንዱን አራቱንም ሌንሶች የተናጠል ትንታኔ ሲመደመር፥ ይህኛው ምእራፍ የሚያተኩረው በጠቃቀም፥ የብዝሃነት ስብጥር፥ ቅርበት፥ እና በተማሪ ምደባ ዘላቂነት መካከል ባሉት ግንኙነቶች ላይ ነው።

እነዚህን ግንኙነቶች ለመረዳት እንዲያስችል፥ አጠቃቀምን፥ የብዝሃነት ስብጥርን፥ እና ቅርበትን ሚዛናዊ በማድረግ መሰል ምናባዊ የት/ቤት ማካለል በመገንባት የሚኖረውን ተጽእኖ የሚያመለክቱ ሞዴሎችን ገንብተናል።

ሞዴሎቹ እንደሚከተሉት ላሉ ጥያቄዎች የሚሰጡ ግምቶችን እንድንረዳና የሚያስከትሉ ተጽእኖዎችን ግምት ውስጥ እንድናስገባ ረድተውናል፦

- ምን ዓይነት ማሻሻያዎችን (በተወሰኑ መመዘኛዎች ውስጥ) ማሳካት ይቻላል?
- MCPS ብዙ ምክንያቶችን በአንድ ጊዜ ማሻሻል ይችላል (ለምሳሌ፦ የትምህርት ቤትን ርቀት መቀነስ እና አጠቃቀምን ማሻሻል፤ ወይም በቅርበት የሚገኙ ትምህርት ቤቶች መካከል ያለውን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንዲሁም የብዝሃነት ስብጥር ልዩነትን በመቀነስ አጠቃቀምን ያሻሽላል?)
- እነዚህ ማሻሻያዎች በሚደረጉበት ጊዜ ከማካለል ጋር በተያያዙ ለውጦች ምክንያት በምን ያህል ተማሪዎች ላይ ተጽዕኖ ያደርግባቸዋል?

እነዚህን ጥያቄዎች ለመመርመር ሞዴሎችን እንደ መሣሪያ አድርገን በመጠቀም በአጠቃቀም፣ በምደባ፣ በተቀራራቢነትና በልዩነት መለኪያ MCPS ውስጥ ያለውን ችግር በተሻለ ሁኔታ መገመት እንችላለን። በዚህ ሪፖርት ላይ የተገመገሙት አምስቱ ሞዴሎች፦

- አጠቃቀም A: ባሉት ክለስተር ክልሎች አጠቃቀምን ማሻሻል
- አጠቃቀም B: በአጎራባች ትምህርት ቤቶች መካከል አጠቃቀምን ማሻሻል (ያሉትን የክለስተር ክልሎች አይጠብቅም)
- የብዝሃነት ስብጥር: የተጨናነቀ አጠቃቀምን በመቀነስ የስብጥር አለመመጣጠንን ማስተካከል
- ቅርበት A: የተጨናነቀ አጠቃቀምን ለመቀነስ ከትምህርት ቤት ያለውን ርቀት ቅድሚያ መስጠት
- ቅርበት B: ከትምህርት ቤት ያለውን ርቀት አሟጦ የመጠቀምን ሁኔታ ማሻሻል

ሞዴሎቹ እንደሚያረጋግጡት በወቅቱ ያለውን የትምህርት ቤት ቅርበት፣ የምደባ ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞችን በማሻሻል በርካታ ወሳኝ የሆኑ ጉዳዮችን ለማሻሻል የሚያስችሉ የወሰን እቅዶችን ማውጣት እንደሚቻል ያሳያሉ።

ክፍል 2፦ የት/ቤት ማካለል ሞዴሎች የእኛን ስልቶች ይዘረዝራሉ፣ አንድ ሞዴል ምን እንደሆነ እና እንዴት እንደሚሰራ በጥልቀት ያብራራሉ፣ እና ከዚህ ትንታኔ ውስጥ ቁልፍ የሆኑ ግኝቶችን ይገልጻሉ።

## ተግባራዊነት

የምዕራፍ 2 (Phase 2) የአሰራር ሂደት የተቀረፀው በምዕራፍ 1 (Phase 1) ወቅት ከማህበረሰብ ተሳትፎ በተገኘ ግብአት እና በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ወቅት በተከሰቱ ጠንካራ ተፅእኖ ነው። የክልል ጥናቱ ቅኝት የመረጃ ልውውጥ "Interactive Boundary Explorer (IBE)" ሒደቱ ማዕከል የኦንላይን መድረክ ተጠቃሚዎች ስለ አዋሳኝ ክልል ትንተና እና ቁልፍ የሆኑ ሌንሶችን ይበልጥ ግንዛቤ እንዲኖራቸው እና ካርታዎችን/ማፖችን፥ ሠንጠረዦችን፥ እና ሌሎች የመረጃ ቋቶችን በመጠቀም መረጃዎችን/ዳታ እራሳቸው መቃኘት ያስችላቸዋል። IBE ሥራ ላይ የዋለው ቨርቹወል ተሳትፎን ለማፋጠን እና በበይነመረብ የማህበረሰብ ዳሰሳ ግብአትን በቀጥታ ለመሰብሰብ በመሣሪያነት ለመጠቀም ነው።

በምእራፍ 1 (Phase 1) የዳሰሳ ወቅት በርካታ ተሳታፊዎች በዚህ ሒደት ስለ ውሂብ/ዳታ ተደራሽነትና ግልጽነት አስፈላጊነት በአጽንኦት አንስተዋል። አንዳንዶቹ በምእራፍ 1 (Phase 1) ትንተና የተደረገባቸውን የዲስትሪክቱን አጠቃላይ አቅጣጫ ስለ ትምህርት ቤቶቻቸው አኃዛዊ መረጃዎችና በሲትሪክቱ ስለሚገኙት ሌሎች ትምህርት ቤቶች ተጨባጭ መረጃዎችን ራሳቸው ለማገናዘብ የሚችሉበትን የመረጃ ልውውጥ ተደራሽነት ጥያቄ አቅርበዋል። የዚህን ምላሽ ለመስጠት ተጠቃሚዎች በዲስትሪክቱ ስለሚገኙት ማናቸውም ትምህርት ቤቶች በቀላሉ ስታትስቲክስ ለማየት እንዲችሉ፣ እና እነዚያን አኃዛዊ መረጃዎች ከክለስተር እና ዲስትሪክት አቀፍ አማካይ መረጃዎች ጋር ማነፃጸር እንዲችሉ፥ እንዲሁም በዲስትሪክት አቀፍ የተደረጉትን የመረጃ ትንታኔዎች ማገናዘብ እንዲችሉና ባለድርሻ አካላት በአሁኑ ወቅት ያለውን የ MCPS ማካለል-ወሰኖችን በሚመለከት ከራሳቸው ተሞክሮ ጋር እያወዳደሩ መመልከት እንዲችሉ IBE ተሻሽሎ ቀርቧል።

IBE ከግለሰብ ተጠቃሚዎች ጋር በተናጠል ከሚሰጠው አገልግሎት በተጨማሪ፣ የሁለተኛው ምእራፍ (Phase 2) አገልግሎት ሂደት የሚከተለውን ያካትታል፡-

- ሁለት የማህበረሰብ ዌብናሮች "Two public webinars" (ኦክቶበር 20 እና 22)
- አንድ አካባቢያዊ ቨርቹወል የማህበረሰብ ውይይት (ኦክቶበር 28)
- አምስት ተገቢ ውክልና ከሌላቸው ማህበረሰቦች ጋር አነስተኛ የቡድን ስብሰባዎች
- የተማሪዎች ተሳትፎ፡- ሦስት አጫጭር ተሳትፎዎች፥ እና ቨርቹወል የውይይት ኩነቶች

የኮቪድ-19 ወረርሽኝ በዚህኛው የተሳትፎ ወቅት ውጥረቶችንና ተግዳሮቶችን አስከትሏል። የቨርቹወል መረጃ ልውውጡ በመሣሪያነት ተሳታፊዎችን ያለስጋት እና ያለ አካላዊ ንክኪ ለመሳተፍ አስችሏቸዋል። ይህ መገልገያ የተሠራው ቀጥታ ለሚደረጉ ስብሰባዎችና ዳሰሳዎች ላይ በመሳሪያነት ጥቅም ላይ እንዲውልና በአቀናባሪ ድጋፍ ከሚመሩ ስብሰባዎች መገልገያነት ይልቅ በተናጠል ራስን ችሎ ስብሰባዎችን ለመሳተፍ የሚያስችል መድረክ እንዲሆን የተዘጋጀ መሣሪያ ነው። የተጠቃሚ ግብዓትን ለመሰብሰብ እንደ ቪዲዮዎች፣ በአቀናባሪ የሚካሄዱ ተሞክሮዎች፣ እና የዲጂታል ዳሰሳ የመሳሰሉ መተግበሪዎች ታክለውበታል።

የመረጃ ልውውጥ መሣሪያው ዲዛይን በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ወቅት በጤንነት እና ደኅንነት ላይ የተደቀኑ ስጋቶችን ለማቅለል ጥቅም ላይ ለማዋል ቢቻልም፥ መሣሪያውን ተገቢ ውክልና ለሌላቸው የማህበረሰብ ቡድኖች ለማዳረስ እና እንዲሳተፉ ለማድረግ በወረርሽኙ ምክንያት አዳጋች ሆኗል።

ይህ የማሳተፍ ሂደት ዝቅተኛ የቴክኖሎጂ ተደራሽነት ላላቸው ማህበረሰቦች፣ እና/ወይም በኦንላይን መረጃዎችን ለመዳሰስና ለመቃኘት አነስተኛ እውቀት ኖሯቸው ምቾት ለማይሰማቸው የማህበረሰብ አባላት እንቅፋት ሆኗል።

በምእራፍ 1 (Phase 1) የዳሰሳ ጥናት በተካሄደበት ወቅት ኢላማ የተደረገባቸው አንዳንድ የህብረተሰብ ክፍሎች እንደገለጹት፣ ከእኛ ጋር በቅንጅት ከሚሰሩት (ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ቤተሰቦች፣ ከሌላ አገር የመጡ ስደተኛ ማህበረሰቦች፣ እና በዝርያ አነስተኛ ቁጥር ያላቸው የማህበረሰብ ክፍሎችን ጨምሮ) ነዋሪዎች ከኮቪድ-19 ወረርሽኝ ጋር ተያይዘው ባሉት በርካታ ችግሮችና ውጥረቶች የትምህርት ቤቶች እንደገና መከፈት ሲጨመርበት መጨናነቃቸውን ሪፖርት አድርገዋል። ይህ ሁኔታ በአነስተኛ ቡድን በሚደረጉ ስብሰባዎች ላይ ጥቂት ሰዎች ብቻ እንዲሳተፉበት አስተዋጽኦ ሳያበረክት አልቀረም።

ከ IBE የተገኘው የዳሰሳ ጥናት መረጃ ስለ ተሳታፊዎቹ ከትምህርት ቤት ክልል ጋር በተያያዘ ቅድሚያ ስለሚሰጧቸው ነገሮች እንዲሁም ከፍተኛው ተፈታታኝ ሁኔታዎች የት እና ምን እንደሆኑና ለማሻሻልም ያሉትን እድሎች ጭምር ያላቸውን አስገራሚ ግንዛቤ ይገልጻል። የ IBE ሪሶርሶቹ በሚገባ ጥቅም ላይ ውለዋል፦ በሺዎች የሚቆጠሩ ተጠቃሚዎች ግንዛቤ እንዲያገኙ የተለቀቁ ቪድኦዎችን በድረ ገጹ ላይ ተመልክተዋል፣ ከ700 በላይ ሰዎች በመሣተፍ በዌብናር የተሰጡ መግለጫዎችን ተመልክተዋል፣ እንዲሁም ከዲሰምበር 1 ጀምሮ ከ 2,100 በላይ የዳሰሳ ምላሾችን አግኝተናል። ይሁን እንጂ የዳሰሳ ጥናቱ እንዳመለከተው የመገልገያ ተጠቃሚዎች ሙሉ በሙሉ የካውንቲውን ሕዝብ የሚወክሉ ያህል አልነበሩም። ከመልስ ሰጪዎቹ በግምት 54% ነዋሪነታቸው በካውንቲው ደቡብ ምእራብ አካባቢ (Bethesda፥ Chevy Chase፥ እና Potomac)፣ 40% ነጮች/ኮኬዝያን White/Caucasian መሆናቸውን (ሌሎች 29% የዘር ሃረግ አለመግለጻቸውን)፣ እና እጅጉን በርካታ መልስ ሰጪዎች (64%) ቀደም ሲል፥ በአሁን ወቅት፥ ወይም የወደፊት የ MCPS ተማሪዎች ወላጆች መሆናቸውን ገልጸዋል።

በምልመላ ወቅት ከሚያጋጥሙ ችግሮች ባሻገር፥ አካባቢን መሠረት ያደረጉ ውይይቶች እና በአነስተኛ ቡድኖች ከተካሄዱት ውይይቶች፥ እንዲሁም ከ 400 የቨርቹወል ተሳታፊ ተማሪዎች የተገኙ ግብአቶች፥ የቨርቹወል ውይይቶች እና ከ IBE የዳሰሳ ጥናቶች የተገኙትን ግብረመልሶች በማቀናጀት ሲተነተን ይህ አይነቱ የማሳተፍ እንቅስቃሴ በርካታ አስገራሚ ግንዛቤዎችን አስገኝቷል።

በዳሰሳው ላይ ስለተደረጉት የተሣትፎ እንቅስቃሴዎች ይዘት አጠቃላይ ግንዛቤ ማግኘት ይቻላል
ክፍል 3/Section 3 የማህበረሰብ ተሳትፎ፦

## ዋና ዋና (ቁልፍ) ግኝቶች፦ ትንተና

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ነጥቦች የዲስትሪክት አቀፍ ክልል ትንተና ጥናት ከተካሄደባቸው አምስት ሞዴሎች የተገኙ ዋና ዋና ግኝቶች ናቸው። እነዚህ ግኝቶችና ሞዴሎቹ የተቀረጹባቸው ግምቶች በዚህ ሪፖርት ክፍል 2 ውስጥ በዝርዝር ተቀምጠዋል፦ የትምህርት ቤት ክልል ሞዴሎች።

1. በዲስትሪክቱ አጠቃላይ ዒላማ የተደረጉ የማካለል ለውጦችን በማድረግ በአጠቃቀም ላይ ከፍተኛ ማሻሻያዎችን ማድረግ ይቻላል።

- እነዚህን ማሻሻያዎች ከ10% በታች ተማሪዎችን እንደገና ወደ ሌላ ዲስትሪክት በማዘዋወር (redistricting)፥ በስፋት ለሚደረገው የዲስትሪክት ማስተካከል መረጃ ልውውጥ ማሳካት ይቻላል። (ይህንን የሞዴሊንግ አቀራረብ ገጽ ይመልከቱ <?>)። ሞዴል 2 (Utilization B) ከሚጠበቀው በታች ጥቅም ላይ የዋሉ ትምህርት ቤቶችን እና ከፍተኛ መጨናነቅ የሚታይባቸው ትምህርት ቤቶችን ሙሉ በሙሉ ማስወገድ ይችላል።

- ከትምህርት ቤት አቅም በላይ በመመዝገብ ገብተው ከሚማሩ ተማሪዎች ብዛት የተነሣ የተጨናነቀ አጠቃቀምን ለማሻሻል የመፍትሔ ጅማሬዎችን CIP ነቅሶ አውጥቷል። ከ 1-4 ያሉት ሞዴሎች በሙሉ ከ 7.5-10% ተማሪዎች እንደገና በሌላ አካባቢ ድልደላ ከተደረገላቸው፤ የማሻሻያ ካፒታል የሚፈልጉ የበርካታ ት/ቤቶችን ቁጥር የሚቀንሱ የማካለል እቅዶችን አግኝተዋል። ከ 2-4 ያሉት ሞዴሎች ለመካለኛ ደረጃ እና ለከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በሙሉ የካፒታል እርምጃን አስወግደዋል። በጊዜያዊነት በቀረበ ሪፖርት ላይ የቀረበው የዝርዝር ጥናት ትንተና እንደሚያሳየው በ 2019-2020 መረጃ መሠረት፥ ሦስት መካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች እና ስምንት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች በ MCPS ሜትሪክስ መሠረት ካፒታል አክሽን እንደሚያስፈልጋቸው ተመልክቷል። እነዚህ ማሻሻያዎች በአባሪ ገጾች ላይ ጠቅለል ተደርገው ተገልጸዋል <?>።

- በ 1-4 ሞዴሎች ላይ የአንደኛ ደረጃና የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን አማካይ ርቀት የማይል አንድ ስምንተኛውን በመጨመር እና ለከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ከሩብ ማይል ያነሰ በመጨመር ይህንን የአጠቃቀም ዘዴ መተግበር ይቻላል። በአብዛኞቹ ሞዴሎች ላይ የሚታየው የርቀት ለውጥ በጣም ጥቂት ሲሆን ወደ ዜሮ የተጠጋ ነው።

- የትኛውም ዓይነት ሞዴሎች በትምህርት ቤት ብዝሃነት-የስብጥር ልዩነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አልነበራቸውም። በእርግጥ አብዛኞቹ ሞዴሎች ይበልጥ በማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ እና በዘር ሃረግ ተነጥለው ካሉት ትምህርት ቤቶች ውስጥ በአቅራቢያቸው ከሚገኙ ሦስት ትምህርት ቤቶች ጋር በተመሣሣይ ደረጃ እንዲሆኑ በአማካይ ከአንድ እስከ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆነ ፐርሰንቴጅ ፖይንት ስብጥሩ አነስተኛ መሻሻል እንዲኖር ማድረግ ችለዋል።

2. የክላስተር ክልሎች በተለይ በጣም በተጨናነቁ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ያሉ የአቅም ችግሮችን ለመቅረፍ እንቅፋት ናቸው።

- የክለስተር ክልሎች እንዳሉ በሚጠበቁበት ጊዜ (ሞዴል 2 አጠቃቀም B)፣ በከፍተኛ የአጠቃቀም መጨናነቅ ወይም ሳይጣበቡ ዝቅተኛ አጠቃቀም ላይ የሚገኙ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ድርሻ የክላስተር ወሰኖች በሚወገዱበት ጊዜ ከሚያሳየው ዜሮ ልዩነት ጋር ሲነፃፀር 6% በመቶ ነው። የአኃዙ መጠን ለመካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች 8% ሲሆን ለከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች 4% ነው።

- ሁለቱም የአጠቃቀም ሞዴሎች ከትምህርት ቤት ያላቸው ርቀት ተመሳሳይ ነው ማለት ይቻላል፤ ይህም ማለት በክላስተር ላይ የተመሠረቱ ማካለሎች ከትምህርት ቤት አጭር ርቀት እንዲኖር እንደማይረዱ ይጠቁማል። በእርግጥ ሞዴል 4 (ቅርበት A) አሁን ያለውን ክለስተር መሠረት ያደረጉ ማካለሎች ለትምህርት ቤት ቅርበት የማያመች እንቅፋት መሆኑን ይጠቁማል።

3. በአጎራባች ትምህርት ቤቶች መካከል ያለውን ድንበር-ማካለል በማስተካከል የትምህርት ቤት አጠቃቀምና ልዩነቶችን ማሻሻል ይቻላል።

- ሞዴል 3 (የብዝሃነት ስብጥር ልዩነት) ከአምስት ትምህርት ቤቶች ውስጥ ሁለቱን የሚወክሉ በማህበራዊ-ኢኮኖሚና በዘር ሃረግ ተነጥለው የሚገኙ ትምህርት ቤቶችን ስብጥር፣ በአቅራቢያቸው ከሚገኙ አጎራባች ሦስት ትምህርት ቤቶች ጋር በአማካይ ከሁለት እስከ አራት በመቶ ያህል በይበልጥ እንዲመሳሰሉ ማድረግ ተችሏል።
- ይህ የሚጠቅመው የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ዒላማ የተደረገባቸውን የአጠቃቀም መጠን ከ32% በመቶ ወደ 43% በመቶ ከፍ ሲል ብቻ ነው። በመካከለኛ እና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ደረጃዎች ሞዴል 3 አነስተኛ የአጠቃቀም ደረጃ እና በጣም የተጨናነቀ አጠቃቀም ያላቸው ትምህርት ቤቶችን ሙሉ በሙሉ ማስወገድ ይችላል።
- እነዚህ ጥቅሞች ሊገኙ የቻሉት ከ7.5 እስከ 10% በመቶ የሚሆኑትን ተማሪዎች እንደገና በመደልደል ትምህርት ቤት ለመድረስ በሚያስችላቸው ርቀት ላይ መጠነኛ ለውጥ በማድረግ ነው። በሞዴል 3 መሠረት የትምህርት ቤት ርቀት በአማካይ (የብዝሃነት-ስብጥር ልዩነትን) ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አንድ-ስምንተኛ ማይል፣ ለመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አንድ-አስረኛ ማይል፣ እና ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ደግሞ ሩብ-ማይል ይጨምራል።

4. በአምስቱም ሞዴሎች ውጤት መሰረት ሌሎች ሜትሪክሶችን ከማሻሻል ጋር በተለይም አጠቃቀምን በማሻሻል ወደ ትምህርት ቤት ያለውን ርቀት ማሻሻል አስቸጋሪ ነው። በጠቅላላ በትምህርት ቤት ደረጃዎች የዲስትሪክቱ አማካይ የርቀት ጭማሪ እስከ ሩብ ማይል ገደማ መጨመሩን ተመልክተናል፥ ይሁንና በአጠቃላይ ሲታይ ዲስትሪክት አቀፍ የጨመረው አማካይ ርቀት ከአንድ-ስምንተኛ ማይል ያነሰ ነው። ይህ ደግሞ የሚያመለክተው አሁን ያለው የትምህርት ቤት ወሰን-ክልል በሌሎች ሌንሶች ኪሣራ የትምህርት ቤትን ርቀት ሊቀንስ እንደሚችል ይጠቁማል።

- መጠነኛ አማካይ የትምህርት ቤት ርቀቶችን በመጨመር ከፍተኛ የአጠቃቀም እና የብዝሃነት-ስብጥር ልዩነትን ሜትሪክስ ማሻሻሎች ማድረግ ይቻላል። ምንም አይነት ሌላ አዲስ ምደባዎች ሳይደረጉ እና ተጨማሪ ዲስትሪክት አቀፍ የማጓጓዣ አስፈላጊነትን ሳያስከትል እነዚህን ማሻሻያዎች በአጎራባች ትምህርት ቤቶች መካከል ማድረግ ይቻላል።
- በአካባቢው ያለው የትምህርት ርቀት የሚቀንስ ቢሆንም በዲስትሪክት ስኬል መሠረት የትምህርት ቤት አማካይ ርቀት በመጠኑ ይጨምራል ወይም በሁሉም ሞዴል ደረጃዎች ላይ ተመሳሳይ ይሆናል። ይሄ በከፊል የትኛውንም ሞዴል ለማከናወን ዓላማ ከ10% ያነሱ ተማሪዎችን እንደገና ለመመደብ ምክንያት ነው።
- እያንዳንዱ ተማሪ በጣም ቅርብ በሆነው ትምህርት ቤት እንዲማር ለማስቻል ት/ቤቱ በቂ አቅም የለውም። ሁሉም ተማሪዎች በጣም ቅርብ ወደሆነው ት/ቤት ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ለማድረግ እንደገና ድልድል ማድረጉ 18.6% በመቶ ገደማ የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎችን እንደገና መደልደል፣ ከመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች 25.0% በመቶ የሚሆኑትን እንደገና መደልደል፣ እና ከሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ደግሞ 23.8% እንደገና እንዲደለደል ያደርጋል (ሞዴል 5። ቅርበት B). ከፍተኛ መጠን ያለው የተማሪዎች ቁጥር እንደገና ከተደለደለ በኋላ እንኳን በዲስትሪክቱ ውስጥ በአጠቃቀምና በቅርበት አነስተኛ መሻሻል ሊታይ የሚቻለው በመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ብቻ ነው።

5. በአምስቱም ሞዴሎች ላይ ከብዝሃነት ስብጥር አኳያ ጠቀሜታው ሲመዘዘን፥ ትንታኔው የሚያሳየው አሁን ያለው የመካከለኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (ሚድል ስኩል) እና የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ማካለሎች ከት/ቤቶች ርቀት ብቻ ይልቅ የሚፈጥሩት ይበልጡን የተማሪዎችን ስብጥር አለመመጣጠን ነው። በነዚህ ት/ቤቶች ደረጃ የምደባ መዋዡቅ ሊኖር የሚችል ቢሆንም፥ የተማሪዎችን ስብጥር አለመመጣጠን ሜትሪክስ ከማሻሻል በተጓዳኝ ከት/ቤቶች ያለውን ርቀት ጭምር የማሻሻል እድሎች ይኖራሉ።

- ሞዴል 5 (ቅርበት B) የትምህርት ቤት ድንበሮችን ርቀትን ብቻ መሰረት በማድረግ መቀየር የሚያስከትላቸውን ተጽእኖ ውጤቶች ይመረምራል፤ ይህም በከፊል የልዩ ምደባዎች (island assignments) ክንውን እንደተጠበቀ ሆኖ ማለት ነው። ይህ ለውጥ ከተደረገ፥ እጅግ ተነጥለው ለሚገኙ አብዛኛዎቹ የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች (ሚድል ስኩልስ) እና ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ እና በዘር ሃረግ አለመመጣጠን ከአጎራባች ትምህርት ቤቶች ጋር ሲነጻጸር ከ 4 - 6 በመቶ/ፐርሰንቴጅ ፖይንቶች ይቀንሳል።
- እነዚህ በመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት እና በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ደረጃዎች የሚደረጉ የብዝሃነት-ልዩነትን የማመጣጠን ማሻሻያ ለውጦች በተለይ ብዝሃነትን ቅድሚያ ትኩረት ከተሰጠበት ሞዴል 3 (የብዝሃነት ስብጥር-ልዩነት) ሜትሪክስ ላይ ከተደረጉት ማሻሻያዎች ይልቅ ይሰፋሉ። ሞዴል 3 በጣም ለተገለሉ የመካከለኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በአማካይ የ2 እና የ3 በመቶ ማሻሻያዎችን ነጥብ አግኝቷል።
- ይልቁንም፣ ሞዴል 5 (ቅርበት B)፣ ስለ አጠቃቀም እና የምደባ መዋዡቅ እጅጉን የጎላ አሉታዊ ተፅዕኖ አለው። እንዲህ አይነቱን ሞዴል ለመተግበር በጣም ተመራጭ ላይሆን ይችላል። ይሁን እንጂ፥ ናሙናው/ሞዴሉ የተማሪ ስብጥር መመጣጠንን በማሻሻል ረገድ የትምህርት ቤት ርቀትንም ለማሻሻል የሚያስችሉ እድሎች መኖራቸውን አጉልቶ ያሳያል።

6. ከ 1-4 ሞዴሎች ላይ በተደረገው ትንታኔ መሠረት፥ ሁሉንም ነገር ያጠቃለለ፥ በዲስትሪክት አቀፍ ስኬል የሚደረጉ ለውጦች አነስተኛ መጠን ካላቸው በውስን አካባቢ ብቻ ከሚደረጉ ለውጦች የበለጠ መሻሻሎችን ሊያስገኙ ይችላሉ።

- ከ2012 ወዲህ በየትምህርት ቤቱ በማንኛውም ዓመት እስከ 2.5% የሚደርሱ ተማሪዎች የምደባ ለውጥ ተደርጎላቸዋል። ከ2012 እስከ ዛሬ ባሉት አብዛኞቹ ዓመታት ውስጥ ከ1 በመቶ ያነሱ ተማሪዎች ብቻ እንደገና ምደባ ተደልድለዋል። ከምደባ ዘላቂነት አንፃር ተፈላጊ ቢሆንም፣ ይህ እያደገ የሚሄድ እና አካባቢያዊ አሠራር፣ በፍጥነት አመዳደብን ለመቀየርና ለከፍተኛ የአጠቃቀም ተግዳሮቶች በቂ ምላሽ ሊሰጥ አይችልም።
- ከ 1-4 ሞዴሎች ዲስትሪክቱ ያሉበትን ተግዳሮቶች የሚዳስሱ እና ከ ከ10% የማይበልጥ የተማሪዎችን ድልደላ በማድረግ አጠቃቀምን ለማሻሻል ጉልህ እድል የሚሰጡ የወሰን ማካለል መላምታዊ የወሰን ማካለል ትልሞችን እቅድ የሚያመለክቱ ናቸው።

## የሞዴሎች ንፅጽር

**Table 1 በዲስትሪክት አቀፍ አምስት ሞዴሎች የወሰን ጥናት ትንታኔ የተገኘውን ቁልፍ አኃዛዊ መረጃ ጠቅለል አድርጎ ያሳያል።**

**ሞዴሎቹን ለማወዳደር አምስት ገላጭ መደቦችን እንጠቀማለን፡-**

ሠንጠረዥ1— ሞዴል (ናሙና) ጥቅሞችና ተጽእኖዎች

| ሞዴል | አጠቃቀም | የብዝሃነት-ስብጥር | ቅርበት | የምደባ ዘላቂነት |
|---|---|---|---|---|
| 1. አጠቃቀም A | ✚ በመጠኑ የተሻለ<br>የትምህርት ቤት አጠቃቀም<br>• ኤለመንተሪ ት/ቤት 80-130%<br>• መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት 74-120%<br>• ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት 82-122% | ◎ አነስተኛ ለውጥ<br>በአብዛኞቹ የተነጠሉ ት/ ቤቶች የዘር ሃረግ ልዩነት ስብጥር ለውጥ<br>• ኤለመንተሪ ት/ቤት -2 ፐርሰንቴጅ ፖይንት<br>• መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ለውጥ የለም<br>• ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ለውጥ የለም | ◎ አነስተኛ ለውጥ<br>ከት/ቤት አማካይ የርቀት ለውጥ<br>• ኤለመንተሪ ት/ቤት +1/10 ማይል<br>• መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ለውጥ የለም<br>• ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ለውጥ የለም | ~ በመጠኑ የከፋ<br>እስከ 10% የሚደርስ ለውጥ በትምህርት ቤት ደረጃ |
| 2. አጠቃቀም B | ★ በጣም የተሻለ<br>የትምህርት ቤት አጠቃቀም<br>• ኤለመንተሪ ት/ቤት 82-119%<br>• መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት 92-103%<br>• ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት 100-106% | ◎ አነስተኛ ለውጥ<br>በአብዛኞቹ የተገለሉ ትምህርት ቤቶች የዘር ሃረግ ልዩነት ለውጥ<br>• ኤለመንተሪ ት/ቤት -1 ፐርሰንቴጅ ፖይንት<br>• መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት -1 ፐርሰንቴጅ ፖይንት<br>• ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት -1 ፐርሰንቴጅ ፖይንት | ◎ አነስተኛ ለውጥ<br>ከት/ቤት አማካይ የርቀት ለውጥ<br>• ኤለመንተሪ ት/ቤት +1/16 ማይል<br>• መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ለውጥ የለም<br>• ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ለውጥ የለም | ~ በመጠኑ የከፋ<br>እስከ 10% የሚደርስ ለውጥ በትምህርት ቤት ደረጃ |
| 3. ስብጥር-ብዝሃነት | ★ በጣም የተሻለ<br>የትምህርት ቤት አጠቃቀም<br>• ኤለመንተሪ ት/ቤት 80-120%<br>• መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት 89-106%<br>• ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት 97-108% | ★ በጣም የተሻለ<br>በአብዛኞቹ የተገለሉ ትምህርት ቤቶች የዘር ልዩነት ለውጥ<br>• ኤለመንተሪ ት/ቤት -4 ፐርሰንቴጅ ፖይንት<br>• መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት -2 ፐርሰንቴጅ ፖይንት<br>• ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት -3 ፐርሰንቴጅ ፖይንት | ~ በመጠኑ የከፋ<br>ከት/ቤት አማካይ የርቀት ለውጥ<br>• ኤለመንተሪ ት/ቤት +1/8 ማይል<br>• መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት +1/10 ማይል<br>• ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት +1/4 ማይል | ~ በመጠኑ የከፋ<br>እስከ 10% የሚደርስ ለውጥ በትምህርት ቤት ደረጃ |
| 4. ቅርበት A | ★ በጣም የተሻለ<br>የትምህርት ቤት አጠቃቀም መጠን<br>• ES: ኤለመንተሪ ት/ቤት 90-120%<br>• MS: መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት 94-108%<br>• HS: ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት 99-107% | ✚ በመጠኑ የተሻለ<br>በአብዛኞቹ የተገለሉ ትምህርት ቤቶች የዘር ልዩነት ለውጥ<br>• ES: ኤለመንተሪ ት/ቤት -2 ፐርሰንቴጅ ፖይንት<br>• MS: መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት -2 ፐርሰንቴጅ ፖይንት<br>• HS: ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት -1 ፐርሰንቴጅ ፖይንት | ◎ አነስተኛ ለውጥ<br>ከት/ቤት አማካይ የርቀት ለውጥ<br>• ES: ኤለመንተሪ ት/ቤት +1/10 ማይል<br>• MS: መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት +1/32 ማይል<br>• HS: ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት +1/10 ማይል | ~ በመጠኑ የከፋ<br>እስከ 10% የሚደርስ ለውጥ በትምህርት ቤት ደረጃ |
| 5. ቅርበት B | — በጣም የከፋ<br>የትምህርት ቤት አጠቃቀም መጠን<br>• ES: ኤለመንተሪ ት/ቤት 46-158%<br>• MS: መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት 76-120%<br>• HS: ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት 61-142% | ★ በጣም የተሻለ<br>በአብዛኞቹ የተገለሉ ትምህርት ቤቶች የዘር ልዩነት ለውጥ<br>• ES: ኤለመንተሪ ት/ቤት -2 ፐርሰንቴጅ ፖይንት<br>• MS: መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት -5 ፐርሰንቴጅ ፖይንት<br>• HS: ሁለተና ደረጃ ት/ቤት -4 ፐርሰንቴጅ ፖይንት | ✚ በመጠኑ የተሻለ<br>ከት/ቤት አማካይ የርቀት ለውጥ<br>• ES: አንደኛ ደረጃ ት/ቤት -1/32 ማይል<br>• MS: መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት -1/8 ማይል<br>• HS: ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት -1/4 ማይል | — በጣም የከፋ<br>ምደባው በት/ቤት ደረጃ ይለያያል<br>• ES: አንደኛ ደረጃ ት/ቤት 17-18%<br>• MS: መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት 23-24%<br>• HS: ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት 22-23% |

pp = ፐርሰንቴጅ ፖይንቶች

1. ★ በጣም የተሻለ
2. ✚ በመጠኑ የተሻለ
3. ⭘ አነስተኛ ለውጥ
4. ∼ በመጠኑ የከፋ
5. ━ በጣም የከፋ

እነዚህ ረድፎች የሌንሱን አስፈላጊነት በሚመለከት የተሰጡ ብይኖች ሳይሆኑ ካሉት ሁኔታዎችም ሆነ ከሌሎች ሞዴሎች ውጤት ጋር የተዛመዱ ተደርገው ሊታዩ ይገባል። አንድ ሌንስ ከሌላው የበለጠ አስፈላጊ ስለመሆኑ አልተመዘነም እና የሞዴል ንጽጽር ሰንጠረዥ እዚህ አልቀረበም ወይም እንደ አንድ የነጥብ ሜትሪክስ የታሰበ አይደለም።

## ቁልፍ ግኝቶች፦ ተግባር

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ነጥቦች በምዕራፍ 1 እና ምዕራፍ 2 (Phase 1 and Phase 2) በማሳተፍ የዳሰሳ ቅኝት በተደረገበት ወቅት የተገኙ ቁልፍ ግኝቶች ናቸው። እነዚህ ግኝቶች በዚህ ሪፖርት ክፍል 3 ውስጥ በዝርዝር ተዳሰዋል፦ የማህበረሰብ ተሳትፎ.

1. የመረጃ/ውሂብ እና የግልጽነት ተደራሽነት በተሳታፊዎች ዘንድ በጣም ተፈላጊነት አለው።

- በምእራፍ 1 (Phase 1) ወቅት በዚህ ትንተና ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለውን መረጃ/ውሂብ የበለጠ ተደራሽነት እንዲኖራቸው የሚጠይቁ እና እርስበርስ የመረጃ ልውውጥ ለማድረግ የሚያስችል በይነመረብ እንዲፈጠር የተሰነዘሩት ጥያቄዎችና አስተያየቶች "Interactive Boundary Explorer (IBE)" እንዲሠራ ምክንያት ሆኗል።
- የዲጅታል እና የመረጃ/ውሂብ መሣሪያዎች (እና ኮቪድ-19 ያስከተለው ገደብ) ተገቢ ውክልና የሌላቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች ለመድረስ አዳጋች ከማድረጉም በላይ፥ የእንቅስቃሴ አለመመቻቸት፣ የመረጃ/ውሂብ ሊተርሲ/ምቹ አለመሆን፣ እና አካባቢያዊ ተሳትፎ ማድረግ ያልተለመደ በመሆኑ አዳጋች አድርጎታል።

2. በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተገቢ ውክልና የሌላቸውን መድረስ አስቸጋሪ ሲሆን እነርሱ ቅድሚያ የሚሰጧቸው ጉዳዮችም ይበልጥ ውክልና ካላቸው ቡድኖች የተለየ ሊሆን ይችላል።

- አካባቢያዊ በሆኑ ስብሰባዎች እና በ IBE የዳሰሳ ጥናት ላይ አብዛኛዎቹ ተሳታፊዎች ነጮች፥ የደቡብ ምእራብ (Southwest) ዲስትሪክት ነዋሪዎች፥ እና የ MCPS ተማሪዎች ወላጆች ናቸው።
- ተገቢ ውክልና የሌላቸው ዒላማ የተደረገባቸው የማህበረሰብ ቡድኖች ተሳትፎ እንደሚያመለክተው (ይኼውም፦ ላቲኖ/ማህበረሰቦች፣ በስደት የመጡ የማህበረሰብ ቡድኖች፣ አፈካን አሜሪካንስ፣ ዝቅተኛ-እና መካከለኛ ገቢ ያላቸው ቤተሰቦች፣ እና በካውንቲው በአነስተኛ ቁጥር ነዋሪዎች የሆኑ) ቅድሚያ በሚሰጧቸው ጉዳዮች ዙርያ ቁልፍ የሆኑ ልዩነቶች ተስተውለዋል።
- በአነስተኛ ደረጃ ከሚወከሉት ቡድኖች ቁልፍ የሆኑት ልዩነቶች የሚያካትቱት፥ የትምህርት ቤት ክልሎችን በመደበኛነት ዘወትር መገምገም፣ በተጨናነቀ ሁኔታ እና ዝቅተኛ አጠቃቀም ባላቸው መካከል የብዝሃነት ልዩነት አስፈላጊነት ላይ ይበልጥ ትኩረት መስጠት ዋነኛ ልዩነቶች መሆናቸው ተስተውሏል።[1]
- የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በማካለል እቅድ ውስጥ ይበልጥ ዒላማ የተደረገ አሳታፊነትን ማካሄድ ያለበት ሲሆን ይኼውም በሰፋት አካባቢያዊ ማሳተፍ ላይ ብቻ ማተኮር የበርካታ ባለድርሻ አካላት ቡድኖች ሃሳብና አመለካከት ትኩረት ሳያገኝ እንዲዘለል ሊያደርግ ይችላል።

1 በምዕራፍ 1 (Phase 1) የዳሰሳ ጥናት ላይ ከአነስተኛ የቡድን ስብሰባዎች የተገኙትን ዝርዝር አስተያየቶችና ጭብጦች ዝርዝር ዘገባ ለማግኘት በምዕራፍ 1 (Phase 1) ላይ ተጨማሪ መረጃዎችን የያዘ አባሪ ይመልከቱ።

3. ለአብዛኛዎቹ የምእራፍ 2 (Phase 2) ተሳታፊዎች ቅርበት እና ዘላቂነት ያለው ምደባ ቅድሚያ የሚሰጡት ከፍተኛ ትኩረት ነው። በዚህ ሪፖርት ላይ የቀረቡት ሞዴሎች የትምህርት ቤት ምደባን ዘላቂነት በመጠበቅ ለትምህርት ቤት ቅርበትን ማሻሻል አስቸጋሪ እንደሆነ ይጠቁማሉ።

- 87% በመቶ የሚሆኑት መልስ ሰጪዎች IBE የዳሰሳ ጥናት ቅኝት ደረጃ ሲሰጡ "እጅግ በጣም አስፈላጊ" እንደሆነ አቅርበዋል። በዳሰሳ ጥናት ተሳታፊዎች-መልስ የምደባ ዘላቂነት ሌላኛው የቅድሚያ ትኩረታቸው መሆኑን የት/ቤት ክልል ወሰን ለውጥ በማድረግ በት/ቤት ክልል ምክንያት በተማሪዎች ላይ የሚያሳድረውን ተጽእኖ መቀነስን እስከ 82% ደረጃ በመስጠት "እጅግ በጣም አስፈላጊ" ነው ይላሉ (ከ..ገጽ ጀምሮ ያለውን ሙሉውን የዳሰሳ ጥናት ውጤቶች ይመልከቱ <OV>)።

- በዚህ ሪፖርት ላይ ያሉት ሞዴሎች በዘላቂ ምደባና የት/ቤት ቅርበትን በማሻሻል ረገድ በጠንካራ ሁኔታ ልዩነቶችን ማቻቻልና ማጣጣት እንደሚያስፈልግ ይጠቁማሉ፡- ዲስትሪክት አቀፍ የትምህርት ቤቶችን ርቀት ለመቀነስ በርካታ ተማሪዎችን (ወደ 20% ገደማ) እንደገና ድልድል ካልተደረገ በስተቀር የሚቻል አይሆንም።

4. ብዙ ተሳታፊዎች የብዝሃነት-ልዩነትን የማጥበብ መሻሻል ውጤቶችን በአብዛኛው ከትምህርት ቤት የጉዞ ርቀት ጋር አዛምደው ይመለከቱታል። በዚህ ሪፖርት ላይ የቀረቡት ሞዴሎች በአቅራቢያ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች ላይ ርቀት/ቅርበት የጎላ ተጽእኖ ሳይኖረው የብዝሃነት-ልዩነትን ማጥበብና ማሻሻል እንደሚቻል ይጠቁማሉ።

- ከ IBE የዳሰሳ ጥናት ተሳታፊዎች-መልስ ሰጪዎች መካከል--40% የሚሆኑት ነጮች መሆናቸውን እና 54% በካውንቲው ደቡብ ምእራብ (Southwest) ነዋሪዎች ለሆኑት--ብዝሃነት ልዩነት በርካታ ተሳታፊዎች-መልስ ሰጪዎች "በጣም አስፈላጊ ያልሆነ" እርምጃ በማለት (እስከ 36%) አስምረውበታል። በዳሰሳ ጥናቱ ወቅት በተደረገ የተሳትፎ እና ሌሎች ዘይቤዎች የተሰጡት አስተያየቶች ቅርበት እና ዘላቂ ምደባ በከፊል ተያያዥነት እንዳላቸው ይጠቁማሉ(በገጽ..የሚጀምረውን ሙሉውን የዳሰሳ ጥናት ውጤቶች ይመልከቱ <?>።

- በዚህ ሪፖርት ላይ ያሉት ሞዴሎች ስለአጠቃቀም እና የብዝሃነት-ልዩነት አሁን ባለው ቅርበት ላይ ከፍ ያለ ተጽእኖ ሳይፈጥር እና ለተማሪ ምደባ ዘላቂነት ምክንያታዊ የአሠራር ዘይቤን በመከተል ማሻሻል እንደሚቻል አመላክተዋል።

- መታወስ ያለበት፥ በሞዴል 3 ላይ እንደተገለጸው አነስተኛ የትምህርት ቤት ጉዞ ርቀት በመጨመር ብዝሃነትና አጠቃቀም አንድ ላይ ሊሻሻሉ ይችላሉ።

5. የተማሪዎች ተሳትፎን በሚመለከት በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የት/ቤት ወሰን ማካለል እቅድ ላይ የተማሪ ድምፅ አስፈላጊ መሆኑን እና ቁልፍ የሆኑ የተማሪ ቅድሚያ ትኩረቶች እና ተሞክሮዎች እንዲገለጹ አድርጓል።

- በምእራፍ 2 (Phase 2) የዳሰሳ ጥናት ወቅት የተማሪ ተሳትፎ ዋነኛ ትኩረት የተደረገበት ሲሆን፥ በርካታ ተማሪዎች እና የተማሪ ቡድኖች በዚህ ሂደት ላይ ለመሣተፍ ከፍተኛ ፍላጎት እንዳላቸው እና የእነርሱ ሃሳብና አስተያየት ግንዛቤ መወሰድ እንዳለበት በምእራፍ 1 (Phase 1) እና በምእራፍ 2 (Phase 2) አጽንኦት በመስጠት ገልጸዋል።
- የተማሪዎች ውይይት በሚካሄድበት ጊዜ ቨርቹወል በሚያደርጉት ውይይት በዚህ አጠቃላ ሂደት ከሚደረገው ተሳትፎ ጋር ሲነጻጸር፥ ቅርብ ለቅርብ ባሉ ትምህርት ቤቶች መካከል እና በዲስትሪክቱ በጠቅላላ በአጠቃቀም እና በብዝሃነት-ልዩነት ረገድ ያሉትን ልዩነቶች እንደ ቅድሚያ የትኩረት ጉዳይ መታየት እንዳለበት ልዩ የሆኑ ጭብቶች ተገልጸዋል።
- ተማሪዎች በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት ደረጃ የተለያዩ አዳጋች ነገሮች መኖራቸውን ያስገነዘቡ ሲሆን፣ አጠቃቀምን እና የብዝሃነት-ልዩነትን በተመለከተ በአብዛኛው የኤለመንተሪ ትምህርት ቤቶች ከባድ ችግር እንዳለባቸው እና በእነዚህ ሌንሶች የተለየ ትኩረት መስጠት አስፈላጊ እንደሆነ በርካታ ግንዛቤ አስጨብጠዋል። በመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት (ሚድል ስኩል) እና በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ደረጃ፥ ተማሪዎች ትኩረት የሰጡት ስለ ቅርበት ሲሆን በተለይም ከትምህርት ቤት ርቀው የሚኖሩ ጥቂት ሪሶርስ ያላቸው ተማሪዎች ጉዳይ ላይ ነው።

6. የ IBE ዳሰሳ ጥናት ውጤት በዲስትሪክቱ ባሉት መልከዓ ምድራዊ ክልሎች ውስጥ ቅድሚያ በሚሰጣቸው ነገሮች ረገድ ከፍተኛ ልዩነት እንዳለ ይጠቁማል።

- ከደቡብ ምስራቅ/Southeast (Colesville, Fairland, and Burtonsville) እና ከደቡብ/South (Silver Spring, Takoma Park, Wheaton, and White Oak) የተሳታፊዎች ቅድሚያ ትኩረት ሌሎች ሪጅኖች ከሚሰጡት የቅድሚያ ትኩረት ይልቅ በርካታ ተሳታፊዎች-መልስ ሰጪዎች እንደገለጹት በአቅራቢያ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች መካከል የሚታየውን የብዝሃነት-ልዩነትን ማመጣጠን እንደሚያስፈልግ "Balance diversity among nearby schools" ወይም በጠቅላላ ዲስትሪክቱ ውስጥ ከሚደረገው ይልቅ እጅግ በጣም አስፈላጊ መሆኑን፣ አነስተኛ ደረጃ የተሰጠው የትምህርት ቤት ቅርበት ጉዳይም እጅግ በጣም አስፈላጊ መሆኑን፥ እና አብዛኛዎቹ ደግሞ አጠቃቀም ላይ ትኩረት መስጠትን አስፈላጊ እንደሆነ አጽንኦት በመስጠት ገልጸዋል።
- እስካሁን ባለው የዳሰሳ ጥናት ውጤት መሠረት፥ ከሌሎች የማህበረሰብ ስብጥር ዘር/የዘር ሃረግ እና ከ MCPS ሚና/ግንኙነት ምክንያቶች ይልቅ ተሳታፊዎች ቅድሚያ የሚሰጡት ለሪጅን ከፍተኛ ትኩረት የሰጡ ይመስላል።
- ከደቡብ ምእራብ (Southwest,) ውጭ ላሉ ነዋሪዎች በአመዛኙ የተሳታፊዎች ቁጥር ዝቅተኛ በመሆኑ፥ በጠቅላላ በዲስትሪክቱ የማህበረሰብን ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ትኩረቶች ለመረዳት ይበልጥ ምርምር እና ህብረተሰብን መድረስ እንደሚያስፈልግ አስተያየት ተሰጥቷል።